በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሠበር መዝገብ ቁጥር 195656

ሀምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንከር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ከሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ ወ/ሮ የጌራወቅ አንጋጋው

2ኛ ወ/ሮ ትዕግስት አንጋጋው

3ኛ ወ/ሮ በለጡ አንጋጋው

4ኛ አቶ አንበርብር አንጋጋው

5ኛ አቶ ናኦድ አንጋጋው

6ኛ ወ/ሮ አስቴር አንጋጋው

7ኛ አቶ ምኒልክ አንጋጋው

8ኛ አቶ አግደው አንጋጋው

9ኛ ወንደወሰን አንጋጋው

ተጠሪዎች፡- 1ኛ የካ /ክ/ከ ወረዳ 06 አስተዳደር

2ኛ ሲስተር ብርሃኔ ሰማኝ

3ኛ አቶ አስራት ገብረ ቃል

4ኛ ወ/ሮ አሰገደች ደበበ

5ኛ አቶ አምባቸው ታረቀኝ

6ኛ አቶ ደበበ ዘውገ

7ኛ አቶ ተክላይ ካሳ

8ኛ አቶ ገዛኸኝ ሽጉጤ

9ኛ አቶ ካሳ ፍሰሃ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚህ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ የሚመለከት ነው። የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 251007 በቀን ሰኔ 15/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ትዕዛዝ በመቃወም ነው።

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ፍታብሄር ችሎት ባቀረቡት ክስ አውራሻችን ቦታውና አዋሳኙ በክሱ ውስጥ የተገለፀዉን 513 ካ.ሜ የሆነው የቤት ቁጥር 390 ጎን ያለውን ይዞታ በውል ከባለቤቶቹ በመግዛት ለቤተሰቦቻቸው መኖሪያ እንዲሆን አንድ ጣራ ግርግዳ የሚጋሩትን እና በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች በመሥራት እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ አምስቱን ደጃፍ ቤቶች ለተለያዩ ሰዎች ሲያከራዩ ቆይተው እነዚህን ቁጥራቸው ከ391-395 ድረስ ያሉ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ ትርፍ ነው በማለት በመውረስ በህገ-ወጥ መንገድ በመውሰድ ከ2ኛ-6ኛ ላሉ ተጠሪዎች በማከራየት እንዲሁም ቤቱን በእነዚህ ተከራዮች ስም ለማዛወር በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ በመሆኑ፣ 1ኛተጠሪ ቁጥሩ 391Aኤ የሆነው ለልጆች መኝታ ቤት የምንጠቀምበትን አንድ ክፍል ቤት በ1981 ዓ.ም በሩን በመስበር ለ9ኛ ተጠሪ አከራይቶ ያለግባብ ጥቅም እያገኘ መሆኑ፤ እንዲሁም 7ኛ ተጠሪ የ9ኛ ተጠሪ ልጅ በቤቱ እየኖረ የሚገኝ በመሆኑ፤

8ኛ ተጠሪ ደግሞ ለጥበቃ ሠራተኛ የተሠራውን የቤት ቁጥር 39 B በማያውቁት መንገድ በመያዝ እየተገለገለ የሚገኝ መሆኑን በመጥቀስ የቀበሌው መስተዳደር አምስት አባላት ያሉት ቡድን ጥቅምት 20 ቀን 1968 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ 11 ክፍል ቤቶች ለአውራሻችን የተፈቀደ መሆኑን ገልፆ ነገር ግን ጋራዥና የእንጀራ መጋገሪያ ቤቶች በጋራ እንድንጠቀም በመወሰኑ አውራሻችን ውሳኔውን በመቃወም ለመስተዳደሩ የንዑስ ወረዳ 04 አዝማች ቡድን በማቅረብ ኮሚቴው ህዳር 23 ቀን 1968 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔም ትርፍ ናቸው የተባሉት ከመኖሪያ ቤቱ ጋር የተያያዙት አራት ክፍል ቤት ከነሰርቪሱ ስለሆኑ በትርፍነት ስለማይቆጠሩ በይዞታቸው ሥር እንዲቆዩ ሌላ ትርፍ ሆኖ የተገኘውን አራት ክፍል ከነሰርቪሱ እንዲያስረክቡ በማለት የወሰነ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ሊያስረክበን ስላልፈቀደ ቤቱን ለቀው እንዲወጡና ያላግባብ ያገኙትን ገቢ እንዲከፍሏቸው አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች ከ9ኛ ተጠሪ ውጭ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በቀን ሐምሌ 5/2010 ዓ. ም በተጻፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቀወሚያ በማለት አመልካቾች ቤቱ አላግባብ በትርፍነት ተወስዶብኛል የሚሉ ከሆነ ለኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት በሰዓቱ ከሚያቀርቡ በስተቀር ለፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ሊያቀርቡ ስለማይገባ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፤ ክርክር የቀረበባቸውን ቤቶች መንግስት ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ እያስተዳደራቸው የሚገኝ በመሆኑ አመልካቾች ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት ተከራክሯል ። ከ2ኛ-6ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካቾች ቤቶቹ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ለአመልካቾች አባት ተፈቅዶላቸው ባለንብረት የሆኑባቸውን ማስረጃዎች ስላላቀረቡ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸውም ፤ አመልካቾች ቤቶቹ የተወረሱ መሆናቸውን የሚያምኑ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 110/87 በአንቀፅ 3/1/ አግባብ ቤቶቹ የተወረሱት በቀላጤ በመመሪያ ወይም ደግሞ በቃል ትዕዛዝ መሆኑን በማስረዳት ውሳኔ በማሰጠት ያልቀረቡ በመሆኑ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም ተበሎ ውድቅ ይደረግልን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክረዋል፡7ኛ ተጠሪ ደግሞ የቤት ቁጥር 391A አመልካቾች 7ኛ ተጠሪን ሊከሱ የማይገባቸው መሆኑን፤ ቤቱ ውስጥ የሚኖረው በጥገኝነት መሆኑን፤ አሁን 9ኛተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ አስረክቦ የታሸገ መሆኑን ገልጸ ተከራክሯል፡፡ 8ኛ ተጠሪ በበኩሉ የቤት ቁጥር 391B ቤቱን ያገኘው በስጦታ ውል ከአመልካቾች አባት መሆኑን በመጥቀስ ክሱ የቀረበው ከ40 ዓመት በኋላ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ የሚገባ መሆኑን ፤ የቤቱ ግምት በአግባቡ ያልተገመተ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ተመልክቶ ህዳር 5 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይንም ቤቶቹ ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ትርፍ ናቸው በሚል በ1ኛ ተጠሪ ተወርሰው

መያዛቸው በአመልካቾች የታመነ መሆኑን ፤ በመንግስት እጅ ለረጅም ጊዜ የተያዘ ቤት ይመለስልኝ ጥያቄ ለፍ/ቤት የሚቀርበው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተጠቅሶ ከሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ከሆነ ወይም በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት በኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ባለመብትነቱ ተረጋግጦ የተወሰነ ከሆነ ለዚህ ማስረጃ ሲቀርብ መሆኑን አመልካቾች ግን ከሚመለከተው አካል ተረጋግጦ የተሰጣቸው ካርታ መኖሩን ወይም በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ባለመብት የሆኑበትን ውሳኔ አለማቅረባቸውን በመጥቀስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት በብይን ዘግቶታል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱም የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው አመልካች መስከረም 8/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎቱ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም 1ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ ክርክሩ ቁጥራቸው 391-395 እና 390 ኤ፣ 390 ቢ ቤቶችን በተመከተ መሆኑን ገልጾ አቅርቦ እያለ ፍ/ቤቱ የቤት ቁጥር 391 ኤ እና 391 ቢ በሆኑ ቤቶች ላይ ምንም አይነት ክርክር ባልቀረበበት ብይን መስጠቱ ስህተት መሆኑን፣ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የአመልካቾች እንደሆኑ በማስረጃ አስደግፈን አቅረበን እያለ የስር ፍ/ቤት በአዋጁ ቁጥር 47/67 መሰረት ያልተፈቀደ በመሆኑ በፍ/ቤቱ ከሰው ሊጠይቁ አይችሉም ማለቱ ስህተት መሆኑን፣ ጥያቄው ያላግባብ ተወረሰብን ሳይሆን ያላግባብ የተወሰዱ ቤቶች እንዲመለሱ የመፋለም ዳኝነት ሆኖ እያለ፣ በቅፅ 003 ላይ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የወረሰው ከአውራሻቸው ሳይሆን አውራሽ አባታቸውን አስረው ከእናታቸው በማስገደድ መሆኑን በመጥቀስ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ለፍ/ቤቱ ያመለከትን ቢሆንም ማስረጃዎቹ ሳይሰሙ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን፣የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉዳዩ በፕሪቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሊታይ ማለቱ ኤጀንሲው የፈረሰ በመሆኑ ጉዳዩን ያለ ፍትህ የሚያስቀር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ የስር ፍ/ቤት አዋጅ ቁጥር 47/67ን የተረጎመበት አግባብ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤት አላግባብ የተያዘባቸው ቤት እንዲለቀቅላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 እና 110/87 እንዲሁም በሰ/መ/ቁ 31682 በሆነ መዝገብ ከተሰጠ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን ታህሳስ 24/2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ በስር ፍ/ቤት የቀረበው ክስ በፍ/ቤቱ ሊታይ የማይችል ስለመሆኑ በተመሳሳይ ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45161

ቅፅ 10 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት መሆኑን፣ሁሉንም ብይን የተሰጣባቸውን ቤቶች በቃል ክርክር ወቅት አንስተው የተካራከሩበት መሆኑን፣ ለክርክር የቀረቡት ቤቶች በአዋጁ ስላለመወረሳቸው አመልካቾች ማስረጃ ያላቀረቡና 1ኛ ተጠሪ ግን ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን፣ የቤት ቁጥር 391 በአዋጁ 47/67 ከተወረሰ በኋላ ቤቱን ሀእና ለ በማለት በመከፍፈል እያስተዳደረው የሚገኝ መሆኑ ቤቶቹ በመንግስት እንደተወረሰ አመልካቾች ያመኑ መሆኑን በመግለፅ የስር ፍ/ቤት ብይን ሊፀና ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን ከ 2ኛ-6ኛ ያሉ ተጠሪዎች በበኩላቸው የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ቤቶቹ ከተወረሱ 40 ዓመት ስለሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሱ ንብረቶች የባለቤትነት ሁኔታ አጣርቶ የመወሰን ስልጣን የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/1/2/ መሰረት ለኢትዮጲያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መሆኑን፣ ቤቶቹ በአንድ ጣራና ግድግዳ ስር የተሰሩ 5 ደጃፍ ቤቶች መሆናቸውንና የአመልካቾች አውራሽ ትርፍ ቤት ስላለው መርጦ በመውሰድ ሌሎቹ በህጉ መሰረት የተወረሱ መሆናቸውን በመጥቀስ የስር ፍ/ቤት ብይን ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

8ኛ ተጠሪ ጥር 21 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች ቤቱ ከአዋጅ ውጭ ያላግባብ ተወርሶ ከሆነ መብታቸውን ተጠቅመው ስልጣን ለነበረው አካል ያላቀረቡና ያልጠየቁ መሆኑን፣ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ 31682 በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተወርሰዋል ተብለው በመንግስት ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሰረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መውረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ 8ኛ ተጠሪ የያዙት ቤት አባታቸው አቶ ሽጉጤ ቡሌ ከአመልካቾች አባት በስጦታ ያገኙት መሆኑ በቀበሌው ማስረጃ መቀበያ መረካከቢያ ደረሰኝ ላይ በማህተም ተረጋግጦ ማህደር ላይ የተቀመጠ መሆኑን፣ ስለሆነም የሚጠየቁበት አግባብ እንደሌለ ተከራክረዋል፡፡ 7ኛ እና 9ኛ ተጠሪ በፍ/ቤቱ መጥሪያ ቢላክላቸውም መልስ ያላቀረቡ በመሆኑ ችሎቱ በቀን መጋቢት 16 ቀን 2013 በዋለው ችሎት መልስ የማቅረብ መብት ቀሪ በማድረግ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሮአል፡፡ በመሰረቱ ለረዥም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበረን ቤት ይለቀቅልኝ በሚል አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተፈቀደለት ስለመሆኑ ወይም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ

አግኝቶ ባለመብት መሆኑን ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ ከመስረዳት ሸክም ከመክሰስ መብት አንፃር በሰ/መ/ቁ 14094 እና 45161 አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል። ይህንን ማስረጃ የሚሰጠውን በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለውን አካል በተመለከተ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአዋጁ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ወገኝ ጉዳዩን ማቅረብ ያለበት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 110/87 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጡት አዋጅ ቁጥር 193/92 እና 572/2000 የሚያሳዩ ሲሆን በዋነኛነትም የአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀፅ 4/2/ /ሐ/ ከአዋጁ ውጪ የተወሰደን ንበረት ባለቤትነት በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሳኔ የሚሰጠው ይኸው አካል መሆኑ በግልፅ ተመልክቷል።

በዚህ አግባብም በሰበር መዝገብ ቁጥር 30631፤30701 እና በተመሳሳይ መዝገቦች በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔም ለረዥም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበረን ቤት ከአዋጅ ውጪ ወይም በህገ ወጥ መንገድ በመንግስት የአስተዳዳር አካል ተወስዶብኛል በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እንዲሁም ከምርጫ ቤት ጋር በተያያዘ የምርጫ ቤቱን፤ በቀላጤ፣በቃል ትዕዛዝ ወይም በመመሪያ ከህግ ውጪ ተወሰደብኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች መርምሮ የመወሰን ስልጣን ያለው የፕራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ለመሆኑ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል። አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ክሳቸውን ያቀረቡት 1ኛ ተጠሪ ቁጥራቸው ከ391-395 ድረስ ያሉ ቤቶችን ትርፍ ነው በማለት በመውረስ በእገ-ወጥ መንገድ በመውሰድ ከ2ኛ እስከ 6ኛ ለተመለከቱት ተጠሪዎች ማከራየቱን የቤት ቁጥር 391Aን በተመለከተም ከ1981 ዓም ጀምሮ በህገወጥ መንገድ በመውሰድ ለ9ኛ ተጠሪ በማከራየት እየተጠቀመ መሆኑን በመግለፅ ሲሆን አመልካቾች አውራሽ አባታችንን በማሰር እናታችንን በማስፈረም የተዘጋጀ ነው ቢሉም ቁጥራቸው ከ391-395 ያሉት ቤቶች የተረከበበትን በ24/03/1968 ዓም የተዘጋጀውን ቅፅ 003 በማቅረብ ቤቶቹ ለረዝም ጊዜ በአስተዳደር አካሉ ቁጥጥር ስር የቆዩ መሆኑን አሳይቷል።ይህ ከሆነ ደግሞ የስር ፍርድ ቤት አከራካሪዎቹን ቁጥራቸው ከ391-395 የተመለከቱትንና ቁጥሩ 391A የሆነው ቤት አስመልክቶ ለፕራይቬሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ባለመብትነታቸው ተረጋግጦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት በወቅቱ በተቋቋመው አካል ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ በሌለበት በቀጥታ ቤቶቹ በህጉ አግባብ ተወርሰዋል ወይስ አልተወረሱም በማለት የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የአመልካቾችን ክስ ከነዚህ ቤቶች አንፃር ውድቅ ማድረጉ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም።

በ8ኛ ተጠሪ ቁጥጥር ስር የሚገኘውን የቤት ቁጥር 391B በተመለከተ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37281 በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አግባብ ቤቱ ተወርሶ ለረዝም ጊዜ በመንግስት የአስተዳደር አካል ቁጥጥር ስር ለመሆኑ አመላካች ማስረጃዎች ያአልቀረቡ በመሆኑና አመልካቾች ክስ ሲያቀርቡም

ሆነ 1ኛ ተጠሪ መልስ ሲሰጥ በዚሁ አግባብ ያልተከራከረ ሆኖ እያለ 8ኛ ተጠሪም የአመልካቾች አውራሽ ለአባታቸው በስጦታ የሰጧቸው የግል ቤታቸው መሆኑን ጠቅሰው እየተከራከሩ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ቤት አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር ከላይ ከተመለከቱት ቤቶች ክርክር ለይቶ በማየት የግራቀኙ የመፋለም ክርክር በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ ከላይ ከተመለከተው ክርክር ጋር አጠቃልሎ በማየት የአመልካቾችን በቤትቁጥር 391B ላይ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በኮመ/ቁ 134862 በ05/03/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት አከራካሪዎቹን የቤት ቁጥራቸው ከ391-395 የተመለከቱትንና ቁጥሩ391A የሆነውን ቤት አስመልክቶ የሰጠውና እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ251009 በቀን 15/10/2012 ዓም በዋለው ችሎት ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል

2. አመልካቾች በየካ ክ/ከ/ወረዳ 06 የሚገኘውን የቤትቁጥር 391B የሆነውን ቤት አስመልክቶ በ8ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ ጥያቄው ለፕራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ቀርቦ ባለመብትነታቸው ተረጋግጦ ወይም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት በወቅቱ በተቋቋመው አካል ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በሌለበት በቀጥታ ቤቱ በህጉ አግባብ ተወርሰዋል ወይስ አልተወረሱም በማለት የመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት የግራቀኙን የመፋለም ክርክር ውድቅ ማድረጉና ይህ ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መፅናቱ መሰረታዊ የህግ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካቾችና 1ኛ ተጠሪ አከራካሪውንቤት አስመልክቶ ያቀረቡት የመፋለም ክርክር 8ኛ ተጠሪ ካቀረቡት መቃወሚያ በመነሳት መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ341(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኃን ይመለስ፡፡

4. ሚያዝያ 04 ቀን 2013 ዓም በዋለው ችሎት በየካ ክ/ከ/ወ/06 የቤ/ቁ391A እና392 የሚገኙ ቤቶች አስመልክቶ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ታዟል፡፡

5. ግራቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ

<u>ጉዳዩ ተገቢውን እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ